# ያለ ገንዘብም ያለ ዋጋም

ዛሬ ጠዋት፡ ወደ ተበርናክሉ መመለስ በእርግጥ መታደል ነው። አንድ ያሳሰበኝ ነገር... ወንድም ኔቪል ከኋላ ያሉ ብዙዎች እንደማይሰማቸው ተናግሯል። ከኋላ ያላችሁ፡ አሁንስ በደንብ ትሰሙኛላችሁ? መልካም ነው? መልካም። እኔ በመጠኑ—እንዲህ ነኝ፡ መኖሬን እንዲያውቁልኝ ጩኸት የማበዛ አይነት ሰው ነኝ።

2 እና፡ ትዝ ይለኛል በአንድ ወቅት የፐብሊክ አገልግሎት ሰራተኛ በነበርኩ ጊዜ። ወደ ደረጃው እየመጣሁ... ያን ጊዜ ከፍ ወዳሉ ቦታዎች ከመውጣት የተነሣ፡ የጫማ ሚስማሮች ያሉበትን፡ ተለቅ ያሉ ጫማዎች አደርግ ነበርና። እና ደረጃዎቹን እየወጣሁ ነበር። እና ወዳጄ የሆነችው፡ ወይዘሮ ኢሃልት፡ በሰልክ ጣብያው ላይ ነበረች። ሚስተር ጊንተር በደንብ እንደሚያውቃት፡ እርግጠኛ ነኝ። ስለዚህ ኢዲት እንዲህ አለች፡ “ቢሊ፡ እኔ ከገጠሙኝ፡ አጫጭር ወዳጆቹ ሁሉ፡ እንዳንተ አይነት ጫጫታ የሚፈጥር ሰው አይቼ አላውቅም።” ደረጃዎቹ ላይ ስወጣ፡ የጫማ ሚስማሮችን እየተራገጥኩ እወጣ ነበርና።

3 እኔም “ይኸውልሽ፡ ኢዲት፡ እኔ አጭር ሰው ነኝ፡ ስለዚህ እንዲህ ያለ ድምጽ በመፍጠር፡ መድረሴን ለሁሉም ማሳወርቅ አለብኝ፡” አልኳት።

4 ወዲያውም፡ ወደ መደወል ገባሁ። ወንድም ኔቪል ስለ ውድ ወዳጃችን፡ ስለ ወንድም ሮይ ሮበርሰን፡ በመታመሙ ምክንያት፡ ዛሬ ጠዋት ከአግልግሎት እንደቀረ ነግሮኛል። የ... የተተከለ ጥርስ ነበረው። ያም ኢንፌክሽን አስከትሏል፡ እና ትንሽ ትኩሳት ፈጥሮበታል። እና ይመስለኛል፡ ወድያውኑ፡ ያሰወጣዋል። እና ሮይ ለእኛ ለሁላችንም እዚህ አባት ሆኖልናል፡ ስለዚህም እንወደዋለን። እና እንዲህ አልኩት፡ “ወንድም ሮይ፡ አ—አሁን በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ፡ ወደ አገልግሎት፡ እየገባሁ ነው።” “ዛሬ ጠዋት፡ ሁላችንም እንድንጸልይልህ ቤተክርስቲያንን እጠይቃለሁ፡” አልኩት፡ ስለዚህ ነገሩ ሲያልቅ፡ ነገ ህክምና ይደረግለታል። ጥርሱ ተጣሞ፡ ወይም የሆነ ነገር፡ በተሳሳተ መንገድ በቅሏል፡ እና ቆርጠው ማሰወገድ፡ ማውጣት አለባቸው።

5 ወንድም ሮይ፡ ሁላችሁም እንደምታውቁት፡ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጀምሮ፡ በቃ ብዙ ጥይቶች ተመትቶ የቆየ አርበኛ ነው። እና በእግዚአብሔር ቸርነት ባይሆን ኖሮ፡ መኖር እንኳን ባልቻለ ነበር። ከሙታን መካከል፡ ለረጅም ጊዜ ወድቆ ተዘርሮ ቆዬ፥ ክንዶቹ እዚህ ጋር ተቦቅሰው፡ እግሮቹም ተቦቅሶ፡ ሁለቱ ዋና ዋና ነርቮቹ ሞቱ። ሐኪሙም እንዲህ አለ፡ “እሱ በህይወት ከኖረ፡ አንድ እርምጃ በጭራሽ አይራመድም።” በእግዚአብሔር ቸርነት፡ በየቀኑ እየወጣ እና እየወረደ፡ ሁሉንም ነገር ይሰራል። እርሱ መልካም ሰው ነውና፡ እግዚአብሔር መልካም አድርጎለታል፡ እኛም እንወደዋለን። እኛም፡ እ—እኛ ሁላችንም እንደዚህ ነን ማለት አይደለም...

6 በጽድቅ መኖራችን፡ ችግሮች የመከላከል አቅማችን ሙሉ ነው ማለት አይደለም። እውነቱን ለመናገር፡ ችግሮች ሁሉ በመንገዳችን ላይ ያመራሉ

ማለት ነው። “የጻድቃን መከራቸው ብዙ ነውና፡ እግዚአብሔር ግን ከሁሉ ያድናቸዋል።” የከበረው ጎኑ ያ ነው።

7 ስለዚህ ዛሬ ጠዋት፡ ለወንድም ሮይ ልዩ ጸሎት እናደርግለታልን። እዚህ ካላችሁ መካከል፡ አሁንም፡ እንዲጸለይልኝ እፈልጋለሁ፡ በጸሎት ቃል መታሰብ እፈልጋለሁ የሚል ካለ እጠይቃችኋለሁ? እጆቻቸውን ብቻ ካነሡ። በቂ ነው። ጥሩ ነው። ከቻላችሁ፡ በምንጸልይበት ጊዜ፡ ለአንድ አፍታ ብቻ እንቁም።

8 ጌታ ሆይ፡ ዛሬ በሰንበት መጀመሪያ ላይ፡ መጥተናል። እና ፀሐይ አሁን በዓለም ላይ ለመዞር፡ አስቀድመው ለዚያ ለተመደቡት ሁሉ፡ ህይወት እና ብርሃን ለመስጠት መንገዷን ይዛለች። ስለዚህም በጉባኤው መጀመሪያ፡ እኛም የቤተ ክርስቲያንህ አካል ነንና፡ የፈውስ አገልግሎቶችን፡ ለአካል ለስጋዊ ፈውስ እንድናደርግ የተጠሩ ነን፡ ይህም ስለ በደላችን የቆሰለውን በእርሱም ቊስል እኛ ተፈወስንበትን የተባረከውን፡ የጌታችንን ምኞትና ፍላጎት ለመፈጸም፡ እንጠይቃለን፡ በጉባኤው መጀመሪያ፡ በዝማሬዎች፡ ክንፎቹ መዘርጋት ሲጀምር፡ ልቦቻችንም ከፍ ማለት ሲጀምር፡ ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማለዳ፡ የተወደደው፡ ትሁቱ አገልጋይህ፡ ውድ ወንድማችንን፡ ሮይ ሮበርስንን፡ እናስበዋለን። እናም በጦር ሜዳ ህይወቱን እንዳተረፍህለት፡ እና መልካም እንደ ሆንህለት እናውቃለን። ዛሬም ቤተ ክርስቲያን መካፈል እስከማይችል ድረስ፡ በደዌ እየተሰቃየ ነው።

9 እናም፡ ጌታ ሆይ፡ በዮሐንስ በማርቆስ ቤት ይጸልዩ በነበረ ጊዜ፡ እነሆ መልአክ ወደ ወኅኒው ቤት ወረደ፡ በዚያም ጴጥሮስ ታስሮ ነበር፡ በሮቹንም ከፍቶ፡ በምስጢር፡ አሰወጣው።

10 አቤቱ ጌታ ሆይ፡ አንተ አሁንም አምላክ ነህ። እነዚያ መላእክት ዛሬ ጠዋት በአንተ ትዕዛዝ ስር ናቸው። ጌታ ሆይ፡ በዚህ በእግዚአብሔር ቤት፡ እየጸለይን ሳለን፡ መላእክት ወደ ወንድም ሮበርስን ቤት ይውረዱ። ምኞቱ እዚህ ቦታው ላይ መሆን ነው፡ ህመም ግን አዘገየው። የእግዚአብሔርም መላእክት ነጻ ያውጡት፡ በእግዚአብሔር ቤት እንደገና በሰፍራው ይሆን ዘንድ፡ ጤነኛም ያድርጉት።

11 ሌሎችም ታ—ታመው፡ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ አልፈው የመጡ አሉ። እናም አንዲት አሮጊት ሴት፡ ወንበር ልትቀመጥ ስትል፡ እጆቿን ወደ ላይ ሲነሱ፡ እግሮቿም ዳዴ ሲሉ አይተናል። ለመፈወስ፡ ወደ እግዚአብሔር ቤት መጥታለች። ጌታ ሆይ፡ እንደ አንዲት ወጣት ሴት ልምላሜ እና ወጣትነት፡ በእግር እየተራመደች እንድትሄድ፡ ፍቀድ።

12 እጆቻቸውን ያነሱት ሁሉ፡ ብዙዎች ወደ ላይ ያነሱት፡ ምክንያቱም እንዲህ ተብሎ ስለ ተጻፈ ነው፡ አስቀድሞም እንዲህ ተብሎ እንደተጠቀሰ፦ “የጻድቃን መከራቸው ብዙ ነው፡ እግዚአብሔር ግን ከሁሉ ያድነዋል።” ከበሽታና ከመከራ ሁሉ ወደሚያድነን፡ ወደ እምነት ክንድ፡ ዛሬ መብረር ይሁንልን። አገልግሎቱ ሲያልቅ፡ አንድም ደካማ በመካከላችን አይኑር።

13 ጌታ ሆይ፡ የማያምን ሁሉ፡ አማኝ እንዲሆን ፍቀድ። ቃልህን ስናሰላስልም፡ መንፈስ ቅዱስ ወስዶ በልባችን ውስጥ ያኑረው፡ የቃሉም ፍሬ እስኪሆን ድረስ በዚያ ውኃ አጠጣው። ጌታ ሆይ፡ በትህትና አንገታችንን ደፍተን በኢየሱስ ስም ስንጠይቅ፡ ይህን አድርግልን። ኣሜን።

አረፍ አረፍ በሉ።

14 ለዛሬ ጠዋት የአገልግሎቱን መልእክት ከመግባቴ በፊት፡ ትንሽ ጠጋ ብዬ፡ በአእምሮአችሁ ይህን ማስያዝ እፈልጋለሁ። ከእናንተ የዕረፍት ጊዜ ያላችሁ ካላችሁ፡ እና በሚድልታውን፡ ኦሃዮ ከሚደረጉ አገልግሎቶች በአንዱ ላይ መገኘት ከፈለጋችሁ፡ ከሰኞ፡ ከሳምንት ጀምሮ፡ በካምፕ ሜዳ ላይ ይደረጋል።

15 ጂን፡ የካምፑ ሜዳው ስም ታውቀዋለህ? [ወንድም ጂንም "ከሚድልታውን አሥራ ሁለት ማይል ርቀት ላይ ነው፡" አለ።—አርታዒ።] ወንድም ሱሊቫን ጋር። ሚድልታውን ትንሽ ከተማ ናት፡ የጄፈርስንቪል ያህል ትመስለኛለች። የቅርጫት ኳስ ማዕከል ናት። በዚያም ወንድም ሱሊቫን ፓስተር ነው። በዚህ ስብሰባ ውስጥ፡ ስድሳ-እና-ከዚያ በላይ የሆኑ የሙሉ ወንጌል አብያተ ክርስቲያናት የሚተባበሩበት ስለሆነ፡ የካምፑ ሜዳ የት እንደሆነ ይነግሩአችኋል።

16 በካምፑም ብዙ ጎጆዎች ይተከላሉ፡ ስለዚህ ለመምጣት የሚፈልጉትን ሰዎች፡ ማቀናጀት እንዳለብኝ ተነግሮኛል። እናም ስብሰባው ከሰኞ ጀምሮ እስከ ቅዳሜ፡ ለስድስት ቀናት ይዘልቃል። እሁድ ቀን አይኖርም፡ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ምክንያት፡ መደበኛ አገልግሎታቸውን እንዲያደርጉ መሄድ አለባቸውና። ምናልባት፡ በእያንዳንዱ ምሽት፡ የፈውስ አገልግሎት፡ ወይም ለታመሙ ጸሎት ይደረጋል። እና ሁላችሁም ተጋብዛችኋል። ይህም የሚጀምረው ከነሐሴ 10 ቀን፡ እስከ 15ኛው ድረስ፡ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ነው። እና የእረፍት ጊዜ ካላችሁ፡ እና—እና የእረፍት ጊዜአችሁን ከደረስ፡ እና እንደዚህ ባለው መንገድ ለማሳለፍ ከፈለጋችሁ፡ እንግዲህ፡ እናንተን ማስተናገድ ደስታችን ነው።

17 በክርስትና ጥምቀት ያልተጠመቃችሁትን ሁሉ አበረታታችኋለሁ፡ ዛሬ ጠዋት ቆም ብላችሁ አስቡበት። እናም አሁን ይመስለኛል፡ ከአርባ-አምስት ደቂቃዎች በኋላ ለሚከናወነው የጥምቀት ስነ ስርዓት ተዘጋጁ። ያም እዚሁ በቤተክርስቲያን ውስጥ ይሆናል።

18 ሰዎች በክርስትና ጥምቀት እንዲጠመቁ ማበረታታት በጣም እንወዳለን፡ ለመዳን አስፈላጊ መሆኑን እናውቃለንና። ጌታችን ለቤተ ክርስቲያን ያለው የመጨረሻው ተልእኮ፡ የመጨረሻው ተልእኮው፡ የተጻፈ ነውና። ወይም፡ በመጨረሻ፡ ቤተክርስቲያንን፡ እንዲህ ብሎ እንዳዘዘ፡ "ወደ አለም ሁሉ ሂዱ፡ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ። ያመነ የተጠመቀም ይድናል።" ስለዚህ በመጥለቅ መጠመቃችን አስፈላጊ መሆኑን እናውቃለን።

19 እኛም ይህንን አገልግሎት ለእናንተ በማቅረባችን ደስተኞች ነን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ፡ እና ኃጢአተኞችን ለማዳን እንደሞተ በልባቸው ለሚያምኑ ሁሉ፡ እናንተም ያድናቸው ዘንድ ከሞተላቸው አንዱ ናችሁና፥ ስለዚህ ለኃጢአታችሁም ስርየት መጥታችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ልትጠመቁ ያስፈልጋችኋል፥ ኃጢአታችሁ እንደ ተሰረየላችሁ፡ ለዓለም፡ ታውጀላችሁ፡ ከእንግዲህ ወዲህ የጌታ ኢየሱስ ደቀ መዝሙር ለመሆን፡ እንደወሰናችሁ ትናገራላችሁ።

20 የምትሄዱበት ቤተ ክርስቲያን ከሌላችሁ፡ ከእኛ ጋር ህብረት ስታደርጉ ደስ ይለናል። እዚ አባልነት የለንም። ለሁሉም የክርስቶስ አካል፡ ለሁሉም የሐይማኖት ተቋማት፡ የተከፈተ ተበርናክል ነው። እኛ በአጥቢያዎች ህብረት እናምናለን። እና ለሰዎች ሁሉ በሮችን እንከፍታለን፡ ማን ይሁን ምን፡ ቀለም፡

ዘር፡ ወይም የሀይማኖት መግለጫ፡ ሁሉም መምጣት ይችላል። “የተጠማ፡ ይምጣ።” ሌላ ቤተ ክርስቲያን ከሌላችሁ ደግሞ፡ መጥታችሁ ከእኛ ጋር ብትተባበሩ ደስ ይለናል። ምንም የምንቀላቀለው ነገር የለንም። በሮች ሲከፈቱ ገብታችሁ፡ ከእኛ ጋር ህብረት አድርጉ። የሚያስፈልጋችሁ ይህ ነውና፡ እንዲሁ ኑ። በተከፈተ ልብ ኑ፡ ትከሻዎቻችሁን ወደ መንኮራኩሩ አስደግፉ፡ እና ወደ-እግዚአብሔር-መንግስት ስንጓዝ አግዙን። ምክንያቱም፡ ሰዓቷ፡ ልክ እንደ ቀረበች እናምናለን፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገሩት ነገሮች በሙሉ ሊፈጸሙ ነውና።

21 በአንድ ወቅት ክሩሼቭ በተባበሩት መንግስታት ያደረገውን ንግግር ብዙዎቻችሁ ማንበባችሁ ግን፡ ምንም ጥርጥር የለውም፡ በአንድ ወዳጄ ከካናዳ ጋዜጣ ላይ እንደተገለጸልኝ፡ እንዲህ አለ፡ “እናንተ ካፒታሊስቶች፡ አምላክ ካለ ያኔ ድሮ እንዳደረገው፡ መቅደሱን እንደገና መጥረጉ፡ እና ማጽዳቱ አይቀርም፡” ስለዚህ አሁን በመስመሮቹ መካከል ማንበብ ትችላላችሁ፡ “ቤተ መቅደሱን እንደገና ለመጥረግ ተዘጋጅቷል።” የሚያስፈራ ነው፡ ኮሚኒስት እንደዚህ አይነት ነገር መናገር ነበረበትን? ቢሆንም፡ የሆነ ነገር ነበረው። በትክክል። መጀመሪያ ላይ፡ ችግሩ የፈጠሩት፡ ካፒታሊስቶች ናቸው። ካፒታሊስቶቹ እኛው ነን።

22 በቀደም ማለዳ፡ ውዱ፡ የተወደደው ፓስተራችን ወንድም ኔቪል፡ በቴሌቪዥኑ ላይ... ወይም በሬዲዮ ሰርጭቱ ላይ፡ አስተያየት ሲሰጥ ሰምቻለሁ፡ ያም በአእምሮዬ ውስጥ፡ ደጋግሞ ይደውላል። በቃ ልረሳው አልችልም። ትናንት ማታ፡ ለአንድ ጓደኛዬ ጠቀስኩት። ነገሩ እንዲህ ነው፡ እንዲህም ይሆናል... መንፈስ ቅዱስ፡ ከምድር ከተወሰደ በኋላ፡ መደበኛዋ ቤተክርስቲያን፡ ልዩነቱን ሳትገነዘበው እንዲሁ ትቀጥላለች። እናንተስ፡ ይሄን ነገር... ሰንቶች ሰምታችኋል? አይገርምም ወይ? መንፈስ ቅዱስን ስለማያውቁት፡ መቼ እንደሚለያቸው አያውቁም፡ እና ያለምንም ለውጥ እንደ ድሮአቸው ይቀጥላሉ። የመጨረሻው ነፍስ በክርስቶስ አካል ውስጥ በታተመ ጊዜም፡ ምን እንደ ሆነ ስለማያውቁ፡ አዳዲስ ነፍሳትን ለማምጣት ለማምጣት፡ አሁንም ይቀጥላሉ። መደበኛ ሃይማኖታቸውም እንደ ቀድሞው ይቀጥላል። አሁን፡ ለእኔ እንደገባኝ ለእናንተ ላይገባችሁ ይችላል፡ ነገር ግን ያ በእውነት የሚገርም አባባል ነበር። ማለት፡ መንፈስ ቅዱስን መጠማት እስኪተው ድረስ፡ በሐይማኖት ስርዓቶቻቸው፡ እጅግ አርቀው ይጠፋሉ፡ ምክንያቱም ከመጀመሪያ ጀምሮም፡ ምንነቱን አያውቁትም።

23 እግዚአብሔር ምህረቱን ያውርድልን። ወንድሜ፡ በዚህ ህይወት ውስጥ ስኖር፡ መሻቴ ሁሉ፡ እሱ በትንሹም ቢሆን ቢያዝን፡ በልቤ አውቀው ዘንድ ነው። ወይም እሱን የሚያሳዝን ነገር ባደርግ፡ ወዲያውኑ እንዲሰማኝ እፈልጋለሁ።

24 የእሱ አለመኖር፡ ይቅርና፥ እሱ እዚህ ካልመጣ እንኳን እኔም እዚህ መምጣት አልፈልግም። በዚያን ጊዜ መሄድ እፈልጋለሁ፡ አዎን፡ ወዳጄ፡ ያን ጊዜ በምህረት ዙፋን ላይ ደሙ አይኖርምና። ጭጋግ ጭስ እና ድቅድቅ ጨለማ ይሆናልና። በመቅደሱ ውስጥ በዚያን ጊዜ፡ ጉዳያችንን የሚከራከርልን ጠበቃ አይኖርም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ እንደሚል ታውቃላችሁ? መቅደሱ በጢስ ተሞላ። በምሕረት ዙፋን ላይ ደም አልነበረም፡ በዚያን ጊዜ ፍርድ ሆነ።

25 ጌታ ከፈቀደ፡ በዚህ የበልግ ወቅት፡ የጥቂት-ሌሊቶች ሪቫይቫል

ያደርግልናል፡ በቃ በአእምሮዬ አደረግኩት፡ ያንን የራዕይ መጽሐፍ ማጥናት እፈልጋለሁ፡ ጥናት ለማድረግ ያህል፡ ወደዚያ ወደ ራእይ መጽሐፍ፡ መግባት ነው።

26 አሁን፡ ዛሬ፡ ብዙዎች ጸሎት ፈልገው፡ ወደዚህ እንደመጡ አውቃለሁ። ቢሮዬ ዛሬ፡ ይልቁንስ በዚህ ሳምንት ዝግ ነበር። ወዲህ ከመጡ አንዳንድ ሰዎች፡ የጸሎት ዕድል አላገኙም፡ በዚያም፡ ምክንያቱም ወንድሞች፡ ለማረፍ፡ ለጥቂት ቀናት ሄደዋል። ብዙ የሚሠሩት ነገር አለባቸው፡ ከራሳቸው ሥራ በተጨማሪ፡ የተበርናክሉ ስራ፡ የሰልኬን ጥሪዎች እና ሁሉንም ነገር ማቀናጀት ይጠበቅባቸዋል። ይህ ሁሉ ሲሆን ነርቭን ይሰባብራል። ስለዚህ ምክንያቱ ይህ ነው። አንዳንዴ፡ እኔም የሆነ ቦታ መውጣት እንዳለብኝ፡ እና የተለየ ነገር ማድረግ እንዳለብኝ አውቃለሁ፡ እነርሱም፡ እንዲሁ ናቸው። ስለዚህ፡ ደውለውልኛል። እኔም፡ “ምንም ችግር የለውም” አልኳቸው። እና በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ፡ ለታመሙ ሰዎች እንጸልያለን።

27 እና ከእግዚአብሔር ቃል ጥቂት ነገር ብናነብ ይሻላል እላለሁ። አሁን መጽሐፍ ቅዱሶቻችሁን ከያዛችሁ፡ ወደ ኢሳያስ መጽሐፍ እንለፍ። መጽሐፋችሁን ይዛችሁ ስታነቡ ማየት ደስ ይለኛል። አነባለሁ… ካነበብናቸው ከአንድ ወይም ከሁለት ያልበለጡ ቃላት ቢሆኑም፡ ግን፡ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ፡ የማይሞት ቃል ነው። ፈጽሞ ሊያልፍ አይችልም። የኢሳይያስ ምዕራፍ 55፣ ርዕስ፡ “የዘለአለም መዳን።”

> **እናንተ፡ የተጠማችሁ ሁሉ፡ ወደ ውኃዎች ኑ፥ ገንዘብም የሌላችሁ፥ ኑና፡ ግዙ፡ ብሉም፥ አዎን፡ ኑ፡ ያለ ገንዘብም ያለ ዋጋም… የወይን ጠጅና ወተት ግዙ።**
>
> **ገንዘብን እንጀራ ላይደለ? የድካማችሁንም ዋጋ ለማያጠግብ ነገር ለምን ትመዝናላችሁ? ተግታችሁ አድምጡኝ፡ መልካም የሆነውን ብሉ፡ ሰውነታችሁም በጮማ ደስ ይበለው።**
>
> **ጆሮአችሁን አዘንብሉ፡ ወደ እኔም ቅረቡ፥ ስሙ፡ ሰውነታችሁም በሕይወት ትኖራለች፥ የታመነችይቱን የዳዊትን ምሕረት፡ የዘላለምን ቃል ኪዳን ከእናንተ ጋር አደርጋለሁ።**

28 **ያለ ገንዘብም ያለ ዋጋም** በሚል፡ በዚህ ርዕስ ላይ፥ ለተወሰኑ ደቂቃዎች፡ እናገራችኋለሁ።

29 በዘመናችን ብዙ አዝናኝ ነገሮች አሉ። ሰዎችን ሁሉ፡ በሁሉም የዕድሜ ክልል ያሉ ሰዎችን የሚያታልሉ “ደስታዎች፡” ብለን የምንላቸው አባባይ ነገሮች አሉ።

30 ወጣቶችን የሚያባብሉ ነገሮች አሉ፡ ሮክ-ኤን-ሮል የምንላቸው ፓርቲዎች ዘመናዊ ጭፈራዎች አሉ፡ አብረው የሚሄዱ የሙዚቃ አይነቶችም አሉ። እነዚህ ሁሉ፡ የመዝናኛው አባባዮች ናቸው፡

31 አንድ ልጅ በእንዴት ያለ ቤተሰብ ቢያድግ፡ ወይም ምን ያህል ቅን የሆኑ ነገሮችን እንዲያደርግ ተምሮ ቢያድግም ግድ የለኝም፥ ይህ ልጅ የአዲሱን ልደት ልምምድ ካልተቀበለ፡ የሮክ-ኤንድ-ሮል ሙዚቃ ልክ እንደሰማ ትኩረቱን ይማርከዋል። ምክንያቱም፡ በእርሱ ዘንድ፡ በተፈጥሮ፡ የተወለደ፡ ሥጋዊ

መንፈስ አለ። ስለዚህ ዛሬ፡ የዚህን ትንሽ ልጅ መንፈስ ለመማረክ፡ የዲያብሎስ ኃይል እጅግ ታላቅ ነው።

32 እንግዲያውስ፡ አዲስ ልደትን በተቃወሙት ሽማግሌዎች ላይ፡ ይህ እንዴት አብልጦ ይሆን! ምክንያቱም፡ ሕይወታችሁ የሚለወጠው፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ እንደገና መወለድ በመቻላችሁ ብቻ ነው፡ በእናንተ ውስጥ ይህ ለውጥ ካልመጣ በቀር፡ የቱንም ያህል ሃይማኖተኛ ብትሆኑም፡ ተፈጥሮአችሁ አሁንም የአለም ነገሮች ይሆናል። ማምለክ እና ሀይማኖተኛ መሆን ትችላለህ፡ ይሁን እንጂ አሁንም የሚስብህ የሆነ የስህበት ኃይል ይቀራል፡ ምክንያቱም ይህ አሮጌው የሐጢአት ሰው እና ምኞቶቹ ሁሉ ገና ከአንተ አልሞቱም።

33 ነገር ግን አንዴ ክርስቶስ ዙፋኑን በልብህ ውስጥ እንዲያደርግ ፍቀድለት፡ እነዚያ ነገሮች አይረብሹህም። እሱ እጅግ የላቀ ነውና።

34 አሁን ስሙን ስለረሳሁት፡ የሰውየውን ስም መጥቀስ አልችልም፡ ብዙዎቻችሁ ግን ታስታውሳላችሁ። ወንዶቹ ሌሎችን ለማጥቃት፡ የሚያደፍጡበት፡ ሴቶቹም፡ እየዘፈኑ የሚወጡበት ደሴት ነበረ ይባላል። እናም ዘፈኖቻቸው በጣም አስደናቂ ከመሆኑ የተነሣ፡ በመርከቦቹ ውስጥ የሚያልፉ፡ መርከበኞች፡ ወደ ውስጥ ይገቡ ነበር። ከዚያም አድፍጠው የነበሩ ወታደሮች—የሚያልፉትን መርከበኞችን ይይዟቸውና፡ ያርዷቸው ነበር። እናም አንድ ታላቅ ሰው በዚያ ማለፍ ፈለገ። መርከበኞቹንም በግንድ ዘንግ ላይ እንዲያሰሩት፡ እ—እ—እንዲሁም እንዳይጮኽ በማለት፡ አፉ ውስጥ አንድ ነገር እንዲወትፋበት አደረጋቸው፥ እ—እንዲሁም መርከበኞቹ ሲያልፉ፡ እንዳይሰሙት፡ በመርከበኞቹ ጆሮዎች ውስጥ፡ ጥጥ አደረገ። ሴቶቹም እየጨፈሩ፡ እ—እና ጣዕመ ዜማ እያሰሙ፡ እየጮኹም መጡ፡ እና፡ ኦህ፡ እጆቹ የታሰሩበትን ቆዳዎች እስኪያዞራቸው ድረስ፡ እጅግ ድንቅ ነበርና፡ መርከበኞቹን እየጮኸ "ወደዚያ ዙሩ እና ግቡ! ወደዚያ ዙሩና ግቡ!" ይላቸው ጀመር፡ በጆሮዎቻቸው ውስጥ ጥጥ ስለነበራቸው ግን፡ ሊሰሙት አልቻሉም።

35 እናም በኋላ ከዘንጉ-ሊፈቱት፡ ወይም፡ እጁን ሊፈቱበት ወደሚገባቸው ቦታ በመርከብ ደረሰ፡ እርሱም ጥጡን ከጆሮዎቻቸው አነሣላቸው። እዚያም፡ በጎዳናዎች ላይ ሲራመድ ሳለ፡ በመንገድ ላይ ከነበሩት ይልቅ እጅግ የላቀ ሙዚቀኛ ሰማ፡ በዚያም እንደገና ባለፈ ጊዜ፡ "ኦህ፡ ታላቁ አሳሽ ሆይ፡ አሁንም እንደገና በመርከቡ ዘንድ ላይ እናሰርህ ዘንድ ትፈልጋለህን፡" በማለት ጠየቁት?

36 እርሱም፡ "አይ፡ አሁንስ ልቀቁኝ። እነሆ ከእንግዲህ ወዲህ ያ እስከማያስቸግረኝ ድረስ፡ ከዚያ የተሻለ ነገር ሰምቻለሁና" አላቸው።

37 ዳግመኛ-ለተወለደ ክርስቲያንም እንዲሁ ነው። ከሮክ-ኤንድ-ሮል እና ከዚህ አለም መዝናኛዎች በጣም የሚበልጥ ነገር አግኝተዋልና። በመንፈስ ቅዱስ ይዝናናሉ። ዓለም እስክትሞትባቸው ድረስ፡ ይህ ለእነርሱ እጅግ ድንቅ ነው።

38 ነገር ግን ወደዚህ ርካሽ መዝናኛ ስትሄድ፡ ብዙ ገንዘብ መክፈል እንዳለባችሁ ማስታወስ አለባችሁ። የሴት ጓደኛውን ወደ እነዚህ ጨዋታዎች እና ጭፈራዎች፡ እና የመሳሰሉትን የሚወስድ ወጣት፡ ከሳምንት ገቢው እጅግ ብዙውን መክፈሉ አይቀርም። የሳምንት ጭንቀታቸውን ጠጥተው ለማስወገድ፡

ደስታን ፍለጋ ወደ ቢራ ቤት የሚሄዱ አዛውንቶችም፡ ታላቅ ገንዘብ መክፈል ይጠበቅባቸዋል። ከዚያስ ምን ያተርፋሉ? ከልብ ድካም በቀር ምንም አያተርፉም።

39 በተጨማሪም ይህን ልብ በሉ፡ እነሆ አንድ ቀን በእግዚ አብሔር ፊት ትጠየቁበታላችሁ። "የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነውና።" በእነዚህ ነገሮች፡ በምድር ላይ ምንም ትርፍ አይኖራችሁም። አታላይ ብርሃን ነው። መጠጣት ሀዘንን ብቻ ይጨምራል። ኃጢአት በሞት ላይ ሞትን ይጨምራል። የመጨረሻዋ ቼክህ ወደ እሳት ባሕር፡ ለዘለአለም፡ ከእግዚአብሔር ለመለየት ናት። ስለዚህ ትከሰራላችሁ እንጂ፡ አንዳች አታተርፉም።

40 ከዚያም እግዚአብሔር መጥቶ ጥያቄውን ይጠይቃችኋል፡ "ገንዘብህን እርካታ በሌላቸው ነገሮች ለምን አባከንከው? ይሄን ለምን አደረግክ? "

41 ሰው ይህን እንዲሰራ የሚያደርገው ምንድን ነው? ትርፋቸውን ሁሉ እና የሚያገኙት በሙሉ፡ መጠጥ በመግዛት፡ እና ለሚያጫፍሯቸው ሴቶች፡ ልብስ በመግዛት፡ ወይም አንዳንድ ዓለማዊ፡ የፍትወት ደስታዎች ይሸምቱበታል።

42 እኛ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ፡ ወደ እግዚአብሔርም እንድንመጣ ታዝዘናል፡ "የዘለአለም ደስታ እና የዘለአለም ህይወት፡ ያለ ገንዘብም ያለ ዋጋም እንድንገዛ ታዝዝን።"

43 እነዚያ ነገሮች ማርካት አይችሉም፡ መጨረሻቸው የዘላለም ሞት ነው። ስለዚህ ያካበትከውን ሃብት በሙሉ ይጠይቅሃል፡ዋናው ለመባል—ታላቅ ወይም ተጫዋች ለመባል፡ ወይም ቀልደኛ፡ ወይም መሆን የፈለግከውን ለመባል፡ ታዋቂ ሴት ለመባል፡ ወይም ምንም ይሁን ምን ዋጋ ያስከፍላል። ይሄን ለማሣካት፡ ያካበትከውን ሃብት ሁሉ ያስከፍላል። አለ የተባለውን ልብስ መልበስህ፡ እ—እና ዓለም የሚያደርገውን ነገር ሁሉ ማድረግህ፡ የዘላለም ፍርድ ለማጨድ ብቻ ነው።

44 ያን ጊዜ፡ እግዚአብሔርም፡ "ለምን" ይጠይቅሃል? ለምን ተብለን ስንጠየቅ፡ በፍርድ ቀን፡ ምን እንመልሳለን? መልሳችን ምን ይሆን? ራሷን የክርስቲያን ሀገር ነኝ ለምትል፡ ለዚች ዘመናዊት አሜሪካ መልሷ ምን ይሆን? እና በአንድ አመት ውስጥ፡ ለምግብ ከሚያወጡት ይልቅ፡ ለዊስኪ ብዙ ገንዘብ ያጠፋሉ። "ገንዘባችሁን ለምን በዚህ አይነት ነገር ታጠፋላችሁ? " ሆኖም፡ መንግስት በአምስት ዶላር ታክስ ምክንያት፡ ምናልባት ታክሱን ወደ አንድ ተቋም በመላካችሁ ምክንያት ወደ እስር ቤት ሊያስገባችሁ ይችላል ምናልባት አንዳንድ ሚሽነሪ ሰራዎች ላይ፡ ታክስ ለመቀበል ላልተመደበ ተቋም ሊሆን ይችላል። አንድ ቀን እንጠየቅበታለን፡ "ይሄን ለምን አደረከው? "

45 እኛ የክርስቲያን ሀገር ነን፡ እናም በቢሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ወደዚያ ሰዎች ተልከዋል፡ ወዳጅነትን ለመግዛት እየሞከርን ነው። አሁንም እነርሱ እየገለበጡት ነው። ክሩሽቼቭ "እምላክ ካለ፡ ቤተ መንግሥቱን እንደገና ይጠርገዋል፡" ማለቱ ምንም አያስገርምም። አረማውያን በእኛ ላይ ውርደትን ለማምጣት፡ እንደዚህ አይነት ንግግሮች ማድረግ ችለዋል። እንዴት ያለ አስቂኝ ነገር ነው! እራሳችንን ደግሞ ክርስቲያን እንላለን።

46 እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡ "ኑ፡ ያለ ገንዘብም፡ ያለ ዋጋም፡ የዘላለምን ሕይወት ግዙ።" በሕይወት፡ ለዘላለም እንድንኖር፡ እኛም ጀርባችንን ለእርሱ

ስጥተን በፊቱ እንሰቃለን። በዚያ ቀን ምን እናደርጋለን? የሚሆነውስ ምንድነው... ?

47 እግዚአብሔር የምንሠራውን ነገር ከሰጠን፡ ገንዘብም ቢሰጠን፡ ከሰማይ በታችም ባለጸጋ አገር ካደረገው፡ እንግዲያውስ እግዚአብሔር፡ ምን አደረጋችሁበት ብሎ ይጠይቀናል። ገንዘባችንን ለማያረኩን ነገሮች ለምን እናጠፋለን? አገር ብቻ ሳትሆን፡ ግለሰቦችም ይጠየቃሉ፥ ከሳንቲም፡ እስከ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር፡ የሚሰጣቸው ለእያንዳንዳቸው።

48 ሰዎች እርስ በርሳቸው ይገዳደላሉ፦ በጣም በቅርብ ጊዜ፡ በአደን ካምፕ ውስጥ ስለሚሠሩ ሁለት ሰዎች አንድ ጽሑፍ አነበብኩ። አንደኛው አምስት ልጆች ነበሩት፡ ሌላኛው ሁለት ልጆች ነበሩት። እና ከመካከላቸው አንዱ ከሥራ መባረር ነበረበት። እና ሁለት ልጆች የነበሩት፡ ወይም አምስት ያሉት አንዳቸው፡ ሁለት ልጆች ካሉት ይልቅ ሥራውን እንደሚያስፈልገው አሰበ፥ እናም አብሮው ወደ አደን ሄዱና፡ እዚያ ከኋላው ተኩሶ ገደለው።

49 ገንዘብ፡ እንዲህ አይነት አገር፡ ይህ ዓይነት ስሜት፡ ህዝቡን የሚገዛው ይህ አይነት መንፈስ ነው።

50 ስለዚህ ዳግም ልደት ፍጹም አስፈላጊ መሆኑን እናያለን። "ዳግመኛ መወለድ አለባችሁ።" መሆን አለበት። "ወደ እኔ ኑ፡ ያለ ገንዘብም ግዙ።"

51 "ገንዘብ የለኝም፡" ማለት አይጠበቅባችሁም። በነጻ የሚሰጥ ነው። ምንም አይነት ገንዘብ አያስፈልጋችሁም።

52 እኛ አሜሪካውያን ለሁሉም ነገር በራሳችን ዋጋ ለመክፈል በጣም የተጋለጡ ነን። ያም መፈክራችንም ነው። "ዋጋ እንከፍላለን። ገንዘብ እናገኛለን።" ዶላራችንን በሌሎች አገሮች፡ እና በሌሎች፡ ድሃ አገሮች እናፈሳለን። ሲገቡም፡ ቱሪስቶች ሲገቡ ስትመለከቷቸው፡ ሁሉም ምርጥ ላባዎች የለበሱ ናቸው። አሜሪካውያን ያስተናግዱአቸዋል። በእግዚአብሔር ፊት እነዚህ ሁሉ ነገሮች እርኩስ ትርፍ ናቸው። ያም የመንግስተ ሰማያት መንገድ አያስከፍትልንም። በአሜሪካ ውስጥ ላለው ነገር ሁሉ ግን፡ ዋጋ መክፈል ይጠበቅብናል።

53 እራት ለመብላት፡ ወደ ሬስቶራንት ትሄዳለህ። ጠረጴዛው ላይ ለአስተናጋጇ የሚሆን፡ ቲፕ ገንዘብ ካላስቀመጥክላት፡ ከቀጠራት ድርጅት ቢከፈላትም፡ ደሞዝ ብታገኝም እንኳ ፊቷን ትከስክስብሃለች። ቢያንስ'ኮ ከደረሰኛችሁ ውስጥ፡ አሰር ፐርሰንት፡ ወይም ከዚያም በላይ ቢሆን ይሻላል። ካልሰጠሃት ግን፡ አስተናጋጇ ቁልቁል እያየችህ ምን አይነት መናጢ ነው ወይም ች—ችጋራም አድርጋ ትመለከትሃለች። ገንዘቧን እየተቀበለች፡ መሆኑ ነው። ይሄን ማድረግ፡ ውርደትም እና አሳፋሪም ይመስለኛል። እኔ እንደማስበው የአገሪቷ ደካማ ውሳኔ ነው። በፊት፡ ጥሩ ሰዎች፡ ጥሩ ቦታዎች፡ ያንን የማንፈቅድ ነበርን። ነገር ግን ሁሉም ነገር ወደ ታላቅ መንፈስ እየገባ ነው።

54 ለጉዞ፡ በባቡር ላይ እሄድ ነበር። እና አንድ ተሸካሚ... እጄ ላይ ትንሽ ቦርሳ ይዤ ነበርና፡ ሻንጣ ነገር ይዤ ነበር፡ እና ትንሿ ጺም መላጫ ቦርሳም ክንዴ ስር አድርጌ፡ እየተራመድኩ ነበር። ተሸካሚውም ቀርቦ፡ እንዲህ አለኝ፡ "ልሸከምልህ እንዴ? "

55 እኔም፡ “ኡህ፡ እዚሁ ባቡሩ ጋር ነኝ፡ ጌታዬ። በጣም አመሰግናለሁ” አልኩት። ሰላሣ ያርድ፡ ያህል፡ ብቻ ቀርቶኝ ነበር።

56 እርሱም፡ “ልያዝልህ” አለና፡ ትንሿን ዕቃ ያዘና፡ መራመድ ጀመረ።

57 እንግዲህ፡ እሱ ሲመጣ፡ እኔ የመሰለኝ ምናልባት ተ—ተከፍሎት እንደሆነ አውቄአለሁ፡ ቢሆንም እኔም እንዲሁ ግ—ግማሽ ዶላር እሰጠዋለሁ ብዬ አሰብኩ። ምናልባት፡ ዕቃዎቼን ይዞ፡ አንድ ደቂቃ፡ ብቻ ይሆናል፡ የያዘው፥ ባብሩ ወዳለበት ለመድረስ፡ የዚህ ተበርናክል መጨረሻ ድረስ ይሆናል። መጀመሪያ፡ ባቡሩ ላይ ወጣሁና፡ ልክ ወጥቼም ተቀበልኩት። አንድ ግማሽ ዶላር ሰጠሁት።

እርሱም “ቆይ እስኪ!” አለኝ፡

እኔም፡ “ምነው፡ ጌታዬ” አልኩት?

እርሱም “ሶስት ሻንጣዎችን ተሸክሜልሃለሁ!” አለኝ፡

እኔም “አዎን፡ ጌታዬ፡ ልክ ነው። ምነው፡ ችግር አለ′ዴ፡” ብዬ ጠየቅኩት?

58 እርሱም “ዝቅተኛ ክፍያዬ በአንድ ሻንጣ ሃያ-አምስት ሳንቲም ነው። ሌላ ሃያ-አምስት ሳንቲም አለብህ፡” አለኝ።

እያችሁ፡ አሜሪካዊነት ይህ ነው፡ ሁሉም ነገር በዋጋ ነው።

59 መኪና እየነዳህ ድንገት ጉድጓድ ውስጥ ቢወድቅብህ፡ እና ጎትቶ የሚያወጣህ ሰው ታገኛለህ። ለመክፈል መዘጋጀት አለብህ፡ ምክንያቱም ያስከፍሉሃል። ባለ ጎታች ካገኘህ′ማ፡ በአንድ ማይል **እጅግ ብዙ** ያስከፍልሃል። እና ገበሬ ሳይቀር፡ ከአሰር ዘጠኝ ያህል፡ ትራክተሩን ካመጣ፡ ከዚያ የከፋ ይሆንብሃል።

60 ላሰራችሁት ነገር ሁሉ መክፈላችሁ የግድ ነው። ሁሉም ነገር እንዲህ ነው “ክፈል! ገንዘብ! ክፈል! ገንዘብ!”

61 ግን ደግሞ ኃጢአት እጅግ ጥልቅ ወደ ሆነው ጉድጓድ ጣላችሁ! ከዚህ የኃጢአት ጉድጓድ ማን ሊያወጣችሁ ይችላል? የሚያወጣህ በሌለበት ጊዜ ግን፡ እግዚአብሔር ከኃጢአት ጉድጓድ፡ ያለ ገንዘብ፡ ያለ ዋጋ ያወጣሃል።

62 የወደቀውን ነገርህ ለሚጎትትልህ በደንብ ካልከፈልከው፡ ጉድጓድ ውስጥ ትቀራለህ። ወይም ገንዘቡን ታመጣለህ ወይም ጉድጓድ ውስጥ ቀርተሃል።

63 ከመቼውም ጊዜ በላይ እጅግ የከፋው ጉድጓድ ግን፡ ዲያብሎስ እናንተን የጣለበት፡ በኃጢአትና ባለማመን ጉድጓድ ውስጥ ነው። ከዚያም እግዚአብሔር በገዛ ፈቃዱ፡ ያለ ገንዘብ፡ ያለ ምንም ዋጋ ያወጣችኋል። ነገር ግን በኃጢያት እየተንገዳገዳችሁ፡ ጉድጓድ ውስጥ ወድቃችሁ፡ ሰሙን እንኳን አትጠሩትም።

64 እና የወደቀውን ሰትጎትቱት፡ ብዙውን ጊዜ ትልቅ ሰንሰለት ወደ ጉድጓዱ ውስጥ ያስገባሉ፡ በመያዣው ወይም በመሳሰሉት ዙሪያ ይጠመጥሙታል፡ ከዚያም መቧጠት ይጀምራል። የመኪናው ኃይል መጎተት ይጀምራል፡ ሞተሮቹም መስራት ይጀምራሉ፡ ጎትተው ያስወጡኣችኋል።

65 እግዚአብሔር በኃጢአት ጉድጓድ ውስጥ፡ ወደ እርሱ ሰትጮኽ ሰምቶ ባገኛችሁ ጊዜ፡ በእግዚአብሔር ፍቅር፡ በቀራንዮ የተጠቀለለበት ሰንሰለት ልኮ፡ በልባችሁ ላይ ያያይዘዋል፡ የመንፈስ ቅዱስንም ኃይል በዚያ ያኖራል፡ መጎተት

ይጀምራል። እና ምንም አያስከፍላችሁም። አሁንም ከኪስ መክፈል ስለማንችል ጉድጓዱ ውስጥ እንቀራለን። እኛ አሜሪካውያን ከኪሳችን ልንከፍል የምንችል ይመስለናል፡ ግን አንችልም። ያለ ገንዘብም ያለ ዋጋም ነው። በቤተክርስቲያን ውስጥ አትከፍሉም። ኢየሱስ በቀራንዮ ከፍሏል። ሰዎች ግን አፍረውበታል። በራሳቸው መንገድ እንዲሆን ይፈልጋሉ። እግዚአብሔር የምትቀበሉት መንገድ አዘጋጅቷል፡ ከተቀበላችሁት በነፃ ነው።

66 ብዙውን ጊዜ፡ ከጉድጓዱ ውስጥ ሲያስወጧችሁ፡ ሁለመናችሁ ይቆሳሰላል፡ ሆስፒታል መሄድ፡ ይጠበቅባችኋል። እና እናንተን ማከም ከመጀመራቸው በፊት፡ አንድ ነገር ከማድረጋቸው በፊት፡ እንዲህ በማለት ይጠይቃሉ፡ “ሂሳቡን የሚከፍለው ማነው? ቁስሉን ልንሰፋው ከሆነ፡ ዘይት ልንቀባው ከሆነ፡ ከደም መመረዝ ለመከላከል ክትባትን—የምንወጋው ከሆነ፡ ምን ዓይነት ኢንሹራንስ አለህ?” አንድ ነገር ከማድረጋቸው በፊት፡ ገንዘብ ከፊት መኖር አለበት።

67 ጌታችን የፍቅሩን ሰንሰለት በልባችሁ ላይ ጠቅልሎ፡ ከኃጢአት ጉድጓድ ሲያወጣችሁ ግን፡ የተሰበረውን ልብ ሁሉ ይፈውሳል፡ ኃጢአቱን ሁሉ ያስወግዳል። ደረሰኙም ከእንግዲህ ወዲህ እንደማታስበው አድርጎ፡ በመርሣት ባሕር ውስጥ ይጠለዋል። “ኑ፡ ያለ ገንዘብም ያለ ዋጋም።” የቱንም ያህል ብትቆራረጥ፡ የቱንም ያህል ብትቆሳሰል፡ ቤተሰብህ ምንም ቢያደርግ፡ ወይም አንተ ምንም ብታደርግ፡ ምንም አይነት ደረሰኝ የለውም። ጭንቀትን ይፈውሳል፡ ሀዘናቸውን ሁሉ ያስወግዳል። “ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፡ ስለ በደላችንም ደቀቀ፥ የሰላማችን ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።” ሁሉም በነጻ።

68 እኛ በተሳሳተ መንፈስ ስለተገዛን፡ አንቀበለውም። ወደ እውነት ሁሉ በሚመራን፡ በእግዚአብሔር መንፈስ፡ መጽሐፉን እውነተኛ በሚያደርግልን፡ በመንፈስ ቅዱስ ከመገዛት ይልቅ፡ የምንገዛው በአገሪቱ መንፈስ ነው፡ የዓለም መንፈስ ነው።

69 ከተወሰነ ጊዜ በፊት፡ ከማያምን ሰው ጋር እየተነጋገርኩ ነበር። እሱም እንዲህ አለ፡ “እስበው፡ ሚስተር ብራንሃም። ስለዚህ ሁሉ የህይወት ስቆቃ፡ ብቸኛው ነገራችን፡ የምንድንበት ብቸኛው መንገድ፡ በአንዳንድ ጥንታዊ የአይሁድ ጽሑፎች ብቻ ነው።”

70 “ኦህ!” አልኩት፡ “ጌታዬ፡ ምናልባት አንተ ያለህ ያ ብቻ ሊሆን ይችላል፡ እኔ ግን ከዚያ የበለጠ ነገር አለኝ። የጸሐፊው የሚያጸናው፡ እና የተሰፋ ቃልም ሁሉ፡ እውነተኛ የሚያደርግ የእርሱ መንፈስ አለኝ።” ያንን እንዴት መቀበል እንዳለበት እንኳን አያውቅም።

71 አያችሁ፡ መጥታችሁ ያለ ገንዘብ መግዛት፡ ያለ ዋጋም መግዛት ብቻ አለባችሁ። ምንም ወጪ አይጠይቅም። ነጻ ነው “የተጠማ፡ ይምጣ።” እግዚአብሔር ከጉድጓድ ያውጣችሁ።

72 መልካም በሚሏት ደጅ ላይ የነበረው ሰውዬ። ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ፡ እግሩ ሽባ ባደረገው በዲያብሎስ፡ ጉድጓድ ውስጥ የተጣለ ሰው ነበረ። መተዳደሪያው ከሚያልፉ ሰዎች ምጽዋት መለመን ነበር። ጧትም በሩ ላይ ተቀምጦ ሳለ፡ ሁለት የጴንጤቆስጤ ሰባኪዎች ሲመጡ አየ። “ብር የለንም፡”

ብሎ እንድተናገረ፡ ሰባራ ሳንቲም አልነበራቸውም። ሰባራ ሳንቲም ትንሿ የብር ሳንቲም ናት። “ብርና ወርቅ የለኝም።”

73 ሰውዬው እንዲህ ያለ ነገር ሳያስብ አይቀርም ብዬ እገምታለሁ። “ኩባያዬን መዘርጋት አያስፈልገኝም።” ምናልባት ጠርቀም ያለ ገንዘብ ሳይፈልግ አይቀርም። አርባ ዓመቱ ነበር፡ ስለዚህ ምናልባት ጠርቀም ያለ ገንዘብ ሳይፈልግ አይቀርም፡ ምክንያቱም፡ ጉዳቱ፡ ከቁርጭምጭሚቲ አካባቢ ስለነበረ፡ መራመድ እንዲችል፡ ሐኪሙ ጥንድ የእግር ደጋፊ ብረቶች እንዲሰራለት ፈልጓል። እና ምናልባት ሀኪሞቹ ድጋፍ ከመስጠታቸው በፊት፡ ጠረጴዛቸው ላይ የሚያስቀምጥላቸው፡ ገንዘብ ማግኘት ነበረበት። እናም ምንም ለሌላቸው ለእነዚህ የጴንጤቆስጤ ሰባኪዎች ኩባያውን መዘርጋት በእርግጠኝነት አያስፈልገውም። ፍርቱናው፡ ከእነዚህ... ከነዚያ ሰዎች ሰባራ ሳንቲም አገኛለሁ ማለት አይሆንም፡ እጅግ ድሆች ናቸው።

74 ፊታቸውን ሲመለከት ግን! አንዱ፡ ወጣት እና የወጣትነት ቀላ ያለ ፊት ያለው፡ ሌላኛው፡ ፊቱ የተሸበሸበ ሽማግሌ ነበሩ፥ እንደ ዮሐንስ... ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ በሩ ሲወጡ። በዚያ ወጣት ሰው ላይ የሆነ ነገር አይቷል። ያም፡ ቅላቱ ትንሽ ከተለመደው ለየት ያለ ነበረ። የገሊላው ፀሐይ ያቃጠለው የሽማግሌው ዓሣ አጥማጅ ፊት፡ ከመሸብሸቡ እና ከአሳቦቹ ስር፡ “የማይነገር፡ እና በክብር የተሞላ ደስታ” ይታይበታል። ትንሽ የተለየ የሚመስል ነገር አየ።

75 ታውቃላችሁ፡ ክርስትና ለየት ያለ ነገር አለው፡ የተለየ እንዲመስሉ የሚያደርግ ነገር አላቸው። በዓለም ላይ በጣም ቆንጆ ሰዎች ናቸው።

እና ኩባያውን ያዘና ወደ ራሱ መለሣት።

76 ሐዋርያው ጴጥሮስም፡ በዕድሜ የሚበልጥ ስለነበረ፡ እንዲህ አለ፡ “ብርና ወርቅ የለኝም።” በሌላ አነጋገር፡ “እነዚህን ክራንቾች ለመግዛት፡ ምንም ልረዳህ አልችልም። ብርና ወርቅ የለኝም፡ ያለኝን ግን!” ማርና የመዳን ወይን ደስታን ከያዘው ከእርሱ ይገዛ ዘንድ አለውና። ከሁለትና ሦስት ቀናት በፊት፡ አንድ ነገር ከተከሰተበት፡ ከበዓለ ሃምሳው፡ ገና መምጣቱ ነበረ።

77 እና ወጣቱ ልጅም በታላቅ “አሜን” እየተፍለቀለቀ፡ ፊቱን ማየት ጀመረ።

78 ምን ተፈጠረ? ያ የርኅራኄ ማሰርያ፡ “ለታመሙ ሰዎች አዝንላቸዋለሁ፡” ብሎ የተናገረው ያ ፍቅር፡ ያንኑ መንፈስ በሽማግሌው በዓሣ አጥማጁ ልብ ውስጥ ገባ። እንዲህም አለ፡ “ገንዘብን በተመለከተ፡ ምንም የለኝም፡ ነገር ግን ከዝሱ ይልቅ ከሚልዮን ጊዜ በላይ አብዝቶ የሚሻለውን ነገር አንድ ነገር አለኝ። ያለኝን!”

79 አሁን ልብ በሉ፡ ጴጥሮስ አይሁዳዊ ነው፡ በተፈጥሮአቸው፡ ገንዘብ ይወዳሉ፡ ይህ አይሁዳዊ ግን ተቀይሮ ነበር። “ያለኝን፡ እሸጥልሃለሁ፡” አይደለም።

80 ነገር ግን፡ “ያለኝን፡ እሰጥሃለሁ! ያለኝን! በኪሴ ውስጥ ሰባራ ሳንቲም የለኝም። አንድ ዳቦ መግዛት አልችልም። ምንም ነገር መግዛት አልችልም። ሳንቲም የለኝም። ያለኝን፡ መቀበል ከቻልክ ግን፡ ለእኔም ተሰጥቶኛልና እኔም ለአንተ እሰጥሃለሁ።” እኛ የምንፈልገው ያ ነው። “ያለኝን፡ እሰጥሃለሁ።”

“ያለህ ምንድነው፡ ጌታዬ? ”

81 “ያለ ምንም ዋጋ፡ ወተትና ማርን ከሚሸጠው ጋር ቆይቻለሁና። ለአንተ እሰጥሃለሁ። በምላሹም ምንም አትከፍለኝም። መቀበል ከቻልክ፡ እሰጥሃለሁ። እንደሚያስከፍሉ ሳይሆን፡ እንደሚሰጡ።”

82 ምክንያቱም፡ “በነፃ እንደተቀበላችሁ፡ በነጻ ስጡ።” ከሦስት ቀናት በፊት፡ የጌታው ተልእኮ ነበር። “ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፡ ወንጌልንም ስበኩ። ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነም ይፈረድበታል። ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፡ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፥ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፥ የሚገድልም ነገር ቢጠጡ፡ አይጎዳቸውም፥ እባቦችን ቢይዙ፡ አያስቸግራቸውም። በነጻ እንደተቀበላችሁ፡ በነጻ ስጡ።” አይሁዳዊው ተለውጧል።

83 በአሜሪካ ውስጥ የሚያስፈልገን፡ ሃይማኖታዊ ስርዓቶቻችንን የሚተካ የመንፈስ ቅዱስ ለውጥ ነው። “በነጻ እንደተቀበላችሁ፡ በነጻ ስጡ።”

84 “ያለኝን፡ እሰጥሃለሁ፥ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ተነሣና ተመላለስ”፥ እምነት በዚህ ባልተበረዘው የፈጣሪ ስም ላይ! እየዘለለ እና እየፈነጠዘ፡ እግዚአብሔርን እያመሰገነ መሄዱ አያስገርምም!

85 ኦህ፡ ይኸውላችሁ ታላላቅ ነገሮቹ፡ ምናልባት በዚያ ቦታ ለአርባ አመታት ተቆምጦ፡ ለራሱ ክራንች ለመግዛት የሚያስችለው በቂ ገንዘብ ለማጠራቀም ጥሯል፡ ይሁን እንጂ አልቻለም። ነገር ግን እጅግ ባልተጠበቀ ስፍራ፡ እና ባልተጠበቀ ሰዓት፡ እንዲሁም እጅግ ከማትጠብቋቸው፡ ተራ ሰዎች፡ የሚያስፈልገውን አግኝቷል። እግዚአብሔር በዚህ መንገድ ስላደረገው በጣም ደስ ብሎኛል።

86 ሆሊ-ሮለሮች በ-በሚባሉት፡ በተራ ሰዎች ዘንድ፡ ገንዘብ ሊገዛው የማይችለውን፡ የሚያስፈልገኝን ነገር አገኘሁ። ማንበብና መጻፍ በማይችሉ፡ ማሃይሞች፡ የድሃ ልብስ በለበሱ ሰዎች፡ በኔግሮዎች፡ ከጅምሩ፡ በዚያ ወለል ላይ፡ በተለወጠው ያረጀ ሳሎን ላይ፡ ዋጋ አገኘሁ፡ ዕንቍ አገኘሁ፥ ያ ጥቁር ፊት ፊቴን እየተመለከተ፡ እንዲህ አለኝ፡ “ካመንክ በኋላ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለሃልን? ” ኦህ፡ የምፈልገው ነገር ነበር። በእነዚያ ሰዎች መካከል አገኛለሁ ብዬ አልጠበኩም፡ የሚያስፈልገኝ ነገር ግን ነበራቸው።

87 የተባበሩት መንግስታት ዛሬ፡ ያለንን አይቀበሉትም፡ የሚያስፈልጋቸው ግን ያ ነው። ክሩሽቼቭ፡ ሌሎቹ ሰዎች ሁሉ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ ክርስቶስ ያስፈልጋቸዋል። ያም አመለካከታቸውን ይለውጣል። የሚጠሏቸውን፡ ሰዎችን፡ ወንድማማች እንዲሆኑ ያደርጋል። ስግብግብነትን ክፋትን፡ እና ክርክርን ያስወግዳል፥ ፍቅርን እና ደስታን፡ ሰላምን፡ ቸርነትን እና ምሕረትን ያደርጋል።

88 አዎን፡ አንዳንድ ጊዜ የምትፈልጉትን የምታገኙት፡ ባልተጠበቁ ቦታዎች ይሆናል።

89 የእስራኤል ልጆች (በግብፅ ምርኮ ሁሉ) ምን መክፈል ይችሉ ነበር ከንፈራቸው በደማ ጊዜ፡ ምላሳቸው ከአፋቸው በተንተለጠለ ጊዜ ምን በከፈሉ? ከግብፃውያን የበዘበዙትን ወርቅ ሁሉ፡ አንዲት ቀዝቃዛ ውሃ ለመጠጣት በከፈሉ ነበር። የምድረ በዳ አለቆቻቸው ከምንጭ ወደ ምንጭ፡ ከጉድጓድ እስከ ምንጭ እየመሩአቸው ነበር፡ ነገር ግን ሁሉም ደርቀው ነበር።

90 ያን ጊዜ መጣላቸው፡ ያለ ገንዘብም ያለው ዋጋም! ድምፁ ነቢዩን አነጋገረው "ለዓለቱን ተናገረው፡" አለው፡ በምድረ በዳ ካሉት ሁሉ የደረቀውን፡ ከውኃም እጅግ የራቀውን ነገርን ተናገረው አለው። በዚያም ያለ ገንዘብም ያለ ዋጋም፡ ጥማታቸውን አረኩ። "ለዓለቱ ተናገሩት።" ዓለቱን ክፍያ ክፈሉት አይደለም፡ ነገር ግን "ዓለቱን ተናገሩት።"

91 ዛሬ ማታም እርሱ ያ ዓለት ነው። በምታደክም ምድር ላይ እርሱ ኦኣለት ነው። በምታደክም ምድር እየተጓዛችሁ ከሆናችሁ፡ ዓለቱን ተናገሩት። ክፍያ መክፈል አይጠበቅባችሁም፥ ብቻ ተናገሩት። በጭንቅ ጊዜ እሱ ህያው ረዳት ነው። ከታመማችሁ፡ ዓለቱን ተናገሩት። በኃጢአት-በሽታ ከታመማችሁ፡ ከዓለቱን ተናገሩ። ከደከማችሁ፡ ዓለቱት ተናገሩት።

92 እያችሁ፡ የትም ብትሆኑ የሚሆን ይመስላል... እንዲህ ይመስላል፡ ምንጮች በነበሩበት ትንንሽ ሰፍራዎች አሁን ውኃ ካልነበረ፡ በዚያ በተራራው ላይ በነበረው ዓለት ላይ ውኃ ሊኖር አይችልም። እግዚአብሔር ነገሮችን የሚያደርገው ሰው ከሚያሰበው ወደ ኋላ ነው። ዓለቱ፡ በምድረ በዳ እጅግ ደረቅ ሰፍራ ነው፡ ይሁን እንጂ "ዓለቱን ተናገረው፡" አለው።

93 ዛሬ፡ ሰዎች በጣም ተታልለዋል። ሄደው ጸሎት በማሳረጋቸው፡ አንድ ካህን እንዲጸልይላቸው ገንዘብ ስለከፈሉ ብቻ፡ ስለ ነገራቸውን ከፍለው የጨረሱ ይመስላቸዋል። የሆነ ቦታ ትልቅ ቤተክርሰትያን ሰላሰሩ፡ እና አንዳንድ ባለጸጎች ስፖንሰር ያደርጉና፡ ከዚያ በኋላ ሄደው በፍትወት ምኞት ይኖራሉ፡ ለእሱ የሚጸልይለት ሌላ ሰው ካለው፡ ያ ነው ብሎ ያሰባል። እግዚአብሔር ቆሻሻ ገንዘባችሁን አይፈልግም። እሱ የሚፈልገው ለእርሱ መስጠት እና በህይወታችሁ እሱን ማነጋገራችሁ ነው። እግዚአብሔር ገንዘብ ሲሰጣችሁ፡ እርካታ በሌላቸው ነገሮች አታጥፉት። እርካታ ባላቸው ነገሮች አጥፉት። እውነተኛውን እርካታ ግን፡ ከዓለቱ ጋር ካልተነጋገራችሁ በቀር አታገኙትም።

94 ያለ ገንዘብም ያለ ዋጋም፡ ሕይወትን-የሚሰጥ ውኃ አወጣ። ጠጡም፡ ግመሎቻቸውም ጠጡ፡ ልጆቻቸውም ጠጡ፡ አሁንም እሱ በምድረ በዳ የሚፈሰው ምንጭ ነው።

95 ዛሬም በዚች በተዳከመች ምድር፡ ለሚጠፋ ሕዝብ፡ እርሱ ዓለት ነው። "በእርሱ የሚያምን ሁሉ፡ የዘላለም ሕይወት ይኖረዋል እንጂ አይጠፋም።"

96 ልብ በሉ። በየአንዳንዱ ምሽት፡ ሰለ እንጀራ አይጨነቁም። እንጀራቸው በየምሽቱ፡ ትኩስ ሆኖ፡ ይቀርብላቸው ነበር።

97 ዛሬ ዳቦ ፍለጋ እንወጣለን። ለማኝ ከሆንክ፡ ወደ ሱቅ ሄደህ፡ "አንዲት እንጀራ ፈለግሁ፡" ብትሏቸው።

98 እንዲህ ይልሃል፡ "መጀመሪያ፡ ሰሙኒህን፡ አሳየኝ። ዳቦውን ለመግዛት ሃያ-አምሰት ሳንቲም መያዝ አለብህ።"

99 ከዚያ በኋላ ከፍለህሰ ምን ታገኛለህ? ይህም ከምግብ ጉዳይ ትንሹ ነው፡ እና ሰንዴው ሊያመርተው ከሚችለው እጅግ ዝቅተኛውን ነገር ታገኛላችሁ። ቫይታሚኑን በሙሉ፡ እና ይዘቱ ሁሉ—ከውሰጡ ያሰወጡታል፡ ለአሳማዎች ይሰጡታል። ይዘቱን ከሚያቅፈው ጋር አንድ ላይ ከሌላ ነገር ጋር ይደባልቁትና፡ አበጥረው፡ እንጀራውን ይሰሩታል፡ ሲሰራም፡ ብዙውን ጊዜ፡ በቆሻሻ እጅ

ይሰራል። አንዳንዴ፡ እንጀራው ውስጥ የምታገኙትን ነገር ተመልከቱ፡ የጸጉር ጥቅልል፡ አስጸያፊ ነገሮች፡ የአይጥ ቁራጭ፡ እና በመጋገሪያዎች ውስጥ የሚወዳድቁትን ነገሮች። የአባለዘር በሽታዎች ያለባቸው እና ኃጢአተኛ ሰዎች፡ እና ሁሉም ነገር፡ ያቦኩታል። ሲሰራ ብታዩት፡ በጭራሽ አትበሉትም። እናም፡ በዚህ ሁሉ፡ ሃያ-አምስት ሳንቲማችሁን ትከፍላላችሁ ካልሆነ ግን አታገኙትም።

100 እግዚአብሔርም በመላእክት እጅ የተሠራ እንጀራ፥ ያለ ገንዘብም፡ ያለ ዋጋም፡ ዘወትር መገባቸው። እናም፡ ዛሬ፡ ያ እንጀራ የክርስቶስ ተምሣሌት ነው፡ ህይወቱን ለመስጠት፡ ከሰማይ የወረደው፡ መንፈሣዊ ህይወት።

101 እግዚአብሔርም ለልጆቹ፡ ዘወትር፡ አዲስ ልምምድን ይሰጣቸዋል። ታስታውሳላችሁ፡ እንጀራውን ማቆየት ሲፈልጉ፡ ይተላባቸው ነበር።

102 አንዳንድ ሰዎች ሲናገሩ ስትሰሟቸው፡ “ይኸውልህ፡ እኔ... ልንገርህ። እኔ ሉተራን ነኝ። እኔ ፕሪስባይቴሪያን ነኝ፡ ባፕቲስት ነኝ። እኔ ጴንጤ ነኝ፡” ይህ ያረጀ በእጅ-የተሰራ እንጀራ ብቻ ነው። ነገሩ ይህ ነው፡ በሰዎች እጅ የተሰራ፡ እጅግ ቆሻሻ ነው።

103 ነገር ግን ትኩስ የሆነውን፡ የምሥክርነት ልምምድ ስትሰሙ ግን፡ “ዛሬ ጠዋት፡ በጸሎት ላይ ሳለሁ፡ መንፈስ ቅዱስ ነፍሴን በአዲስ መልክ አጠመቀኝ።” ኦህ፡ ወንድሜ ሆይ፡ የመላእክት ምግብ ማለት ይህ ነው። ከሰማይ ሆኖ፡ በየእለቱ፡ ትኩስ ይመግባቸዋል።

የሚያስፈልገንን የበረከት ዝናብ፥
የምህረት ጠል በዙርያችን ነጠብጣብ ሆኗል፡
ጸሎታችን ግን ጅረት ይሁንልን።

104 ኦህ፡ አዎን፡ ጌታ ሆይ፡ የሕይወት እንጀራ የሆነውን፡ ህያው ክርስቶስን፡ ከሰማይ ላክልን። አቤቱ ወደ ልቤ ወርውረው፡ በታላቅ መገኘቱ እደሰት ዘንድ ፍቀድልኝ።

105 እውነት ነው፡ እነርሱ ያመስግኑ ነበር። አመስጋኞች ነበሩ። ከእግዚአብሔር መንፈስ የተወለደ፡ እና መንፈስ ቅዱስን የተቀበለ፡ ወንድ ይሁን ሴት ሁልጊዜ ያመስግናል። ምንም ነገር ቢፈጠር፡ አመስጋኝ ትሆናለህ።

106 ልክ በተራራ ላይ፡ ዓይነ ሰውር ሆኖ፡ እንደተወለደው፡ ትንሹ ቤኒ። በሰምንት ወሩ አካባቢ፡ የዓይን ሞራ ግርዶሽ አይኑን መሸፈን ጀመረ። ወላጆቹም ድሆች ነበሩ። የሚኖሩት ባረጀ ጭቃማ ኮረብታ ላይ ነበር። እና ማየት እንዲችል፡ ኦፕራሲዮን ቢደረግ የህጻኑ ቤኒ አይኖች ሊያድኑት እንደሚችሉ አውቀው ነበር። ከዚያ የአስራ ሁለት አመት ልጅ ሆነ። የወላጆቹ አቅም የዓመት ቀለብ እና እንጀራ መግዛት ብቻ ነበር። ቀዶ ጥገናውን የመሸፈን አቅም አልነበራቸውም።

107 ሁሉም ጎረቤቶች፡ ተሰብስበው፡ ህጻኑ ቤኒ፡ አይነ ሰውር ሆኖ ከህጻናት ጋር ለመጫወት ሲሞክር ያዩት ነበር። የሚያደርገውን ማየት አይችልም ነበር። ሁሉም አዘኑለት። እና እያንዳንዳቸው፡ በዚያ አመት፡ ትንሽ ተጨማሪ ሰብል ሰፍረው አስቀመጡ። በጸሐይ ብርሃን እጅግ በርትተው ሰሩ። በበልግ ወቅት ሰብሉ በተሸጠ ጊዜ፡ ገንዘብ ሰብስበው ህጻኑ ቤኒን ባቡር ላይ አስቀመጡት፡ ወደ ዶክተርም ላኩት።

108 ቀዶ ጥገናውን በተሳካ ሁኔታ አከናወኑት። እሱ በተመለሰ ጊዜ፡ ህጻኑ ቤኒ ከባቡር ሲወርድ ጎሮቤቶቹ ሁሉ በዙርያው ከበቡት። ትንንሽ፡ ብሩህ አይኖቹ ያበራሉ። ፊታቸውን እያየ፡ መጮህ እና ማልቀስ ጀመረ።

109 ከረዳቶች አንደኛው፡ “ልጄ ሆይ፡ ቀዶ ጥገናውን ለማድረግ ስንት ፈጀብህ” በማለት ጠየቀው?

110 እርሱም፡ “ጋሼ፡ ለእነዚህ ሰዎች ምን ያህል ዋጋ እንዳስከፈላቸው እኔ አላውቅም። ይሁን እንጂ እነዚህ ዋጋ የከፈሉትን፡ ፊቶቻቸውን በማየቴ እጅግ ደስ ብሎኛል።”

111 እኛ የሚሰማን እንደዚህ ነው። እግዚአብሔርን ምን ያህል ዋጋ እንደሚያስከፍለው አላውቅም። አለኝ የሚለውን ነገር ለእኔ እንደሰጠኝ አውቃለሁ፡ ልጁን። ይሁን እንጂ መንፈሳዊ እይታ ስለሰጠኝ እጅግ አመሰግነዋለሁ፡ ፊቱን አይቼ እርሱ ስለ እኔ እንደሞተ ማወቅ ችያለሁና። ምን ያህል እንዳስከፈለው እኔ አላውቅም። ይሄን መገመት የምንችልበት መንገድ የለንም። ዋጋው ታላቅ ነው። እንዴት እንደሆነ ልነግራችሁ አልችልም። ይሁን እንጂ አመሰግናለሁ። ምስጋናዬ ብዙ ነው፡ ይህም፡ እዉር ስለነበርኩ፡ አሁን ግን ማየት በመቻሌ ነው።

112 ማዮ ብራዘርስ ጊዜዬ ማብቃቱን ሲነግሩኝ አመሰገንሁ፡ የዛሬ ሃያ-አምስት አመታት በፊት፡ ዶክተሮቹ ከአሁን በኋላ መኖር እንደማልችል ነገሩኝ፡ ዛሬ በህይወት አለሁ። እግዚአብሔርን ምን ዋጋ እንዳስከፈለው እኔ አላውቅም፡ በህይወት በመሆኔ ግን አመሰግናለሁ።

113 ኃጢአተኛ ነበርኩ፡ በኃጢአት የታሰርኩ፡ በልብ ሕመም፡ ሞትን የምፈራ ነበርኩ። ዛሬ፡ ግን፡ ሞት ድሌ ነው። ሃሌ ሉያ! ፊቱን ማየት እንድችል፡ በምወደው በእርሱ ፊት ብቻ ያመጣኛል። ነገሩን ቀይሮ፡ በቀዶ ጥገና ልቤን ወስዶ፡ አዲስ አደረገው። የሆነ ነገር እንደሆነልኝ አውቃለሁ።

114 ባለፈው የበልግ ወቅት፡ በሚኒሶታ በወጣ ጋዜጣ፡ አንድ ትንሽ ልጅ ብስክሌቱን ይዞ አንድ ቀን ጠዋት ወደ ቤተ ክርስቲያን፡ ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት የሄደ ልጅ ነበር። ሌላ የሠፈሩ ወጣት፡ ከሰንበት ትምህርት ቤት ጋር ምንም ጉዳይ አልነበረውምና፡ የሴት ጓደኛውን ወስዶ ስኬቲንግ ለመጫወት ሄደ። እናም ሰውየው ትልቅ ሰው ነበር፡ እና በሰሰ በረዶ ውስጥ ገብቶ ወደቀ። በዚያን ቀን ማለዳ በመንገድ ላይ ሲሄድ አይቶት ህጻኑ ላይ ተሳልቆበት ነበር፡ ሴት ጓደኛውን፡ “ይኸውልሽ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄደውን እክራሪውን ተመልከቺው፡” አላት። እና በበረዶው ውስጥ ሲወድቅ፡ የሴት ጓደኛው ከእሱ ርቃ ነበር። ክብደት ስላልነበራት፡ አርቃ ሄዳለች። ነገር ግን ወደ ላይ ወጥቶ፡ እጆቹን በበረዶ ላይ ሲያደርግ፡ ሸባ ሆኖ በበረዶው ላይ ተንጠለጠለ።

115 የሴት ጓደኛው እሱን ለመርዳት ሞክራ ነበር፡ ነገር ግን በጣም ከብዳበት፡ በረዶውን ልትሰብረው-ሆነች። እርሱም “ተመለሺ! ተመለሺ! ትወድቂያለሽ፡ ሁለታችንም እንሰምጣለን፡” አለና ጮኸባት። ጮኸ፡ አለቀሰ፡ የሚረዳው የለም።

116 ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፡ ከኮረብታው አናት ላይ፡ ትንሿ ብስክሌቱን፡ እየነዳ፡ በእጁ ስር መጽሐፍ ቅዱስ የያዘ ትንሽ ልጅ መጣ። ጩኸቱን ሰምቶ፡ ብስክሌቱን በፍጥነት ነዳት። እና መጽሐፍ ቅዱሱን አስቀምጦ፡ ወደ በረዶው ሮጠ። በለበሰው ቆንጆ ልብስ፡ በትንሿ ሆዱ እንዲህ ተኝቶ፡ የሰውየውን እጅ

መያዝ እስኪችል ድረስ ተሳበ፡ እና ከበረዶው እስኪያወጣው ድረስ፡ ወደ ውጭ ጎተተው። በሩጫ ሄዶ መኪና አስቆመ። አምቡላንስ ጠርተው ወደ ሆስፒታል ወሰዱት።

117 ሄዶ አምቡላንሰን ከከፈለ በኋላ፡ ለዶክተሮቹ የሳንባ ምች ክትባቶችን እና የሚወስዳቸውን ነገሮች ከፍሎ፡ ወደ ትንሹ ልጅ መጣ። እንዲህም አለው፡ “ልጄ ሆይ፡ ዕዳዬ ስንት ነው? ”

ልጁም፡ “ምንም” አለው።

118 እርሱም “እኔ ለአንተ የህይወት ዕዳ አለብኝ፡” አለው። አሰቡት። ህይወቱ ናት። ገንዘብ አይከፍለውም።

119 እኛም ለእግዚአብሔር ሊሰማን የሚገባው በዚህ መንገድ ነው። በሆነ ነገር በራሳችን መንገዳችንን ማበጃጀት አይደለም፥ እኛ ግን እየሞትን በኃጢአት ጉድጓድ ውስጥ እየሰመጥን ነበርና፡ ለእግዚአብሔር ሕይወታችን ዕዳ አለብን። እግዚአብሔር እጆቹን እና መጎናጸፊያውን በላዬ ላይ ጣለ።

በኃጢአት ሰምጬ ነበረ ጠልቄ፡
ከሰላሙ ባህር ዳርቻ ርቄ፡
ከውስጤ በዝገት ተሞልቼ፡
ከእንግዲህ ላልነሣ ሰምጬ፥
የባህር ጌታ ግን
ተሰፋ የቆረጠ ጩኸቴን ሰማ፡
ከውኃውም አነሳኝ፡
አሁን ደህና ነኝ።

120 በህይወቴ ለእርሱ ባለ ዕዳ ነኝ። እናንተም ለእርሱ የህይወት ዕዳ አለባችሁ። እሱን ለማገልገል፡ የህይወት ዕዳ አለባችሁ፥ ለመቅበዝበዝ እና ልትታበዩበት፡ ለሐይማኖት ተቋማችሁ ልትሰጡት አይደለም፥ ሌሎቹን ልትተቹበትም አይደለም፥ ነገር ግን ሌሎችን ለማገልገል እና ለማዳን፡ እና ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ለማምጣት ነው።

121 የጠፋው ልጅ። አሁን በመዝጊያ ላይ፡ ይህን እላለሁ። የነገረውን ሁሉ ካባከነ በኋላ፡ በአመጽ ኑሮ፡ የአባቱም ነገር ካባከነ በኋላ፡ ወደ ቤቱ በሚመለስበት ጊዜ... በአሳማ ጉሮኖ ውስጥ ይተኛ ነበር፡ ከዚያው ወደ ልቡ ተመለሰ። እርሱም “አባቴ፡ በልተው የሚያተርፉ፡ ስንት ቅጥረኛ አገልጋዮች አሉት፡ እነሆ፡ እኔ በችግር ምክንያት እሞታለሁ፡” አለ። እንዲህ ለማለት ቢሞክር ኖሮስ፡ “ገንዘብ ቢኖረኝ ኖሮ (ሰባክን ያጠፋሁትን) መልሼ ለአባቴ እከፍለው ነበር ቢልስ? ” እርሱ ግን የአባቱን ባሕርይ ያውቃል፡ “ተነሥቼ ወደ አባቴ እሄዳለሁ፡” አለ።

122 አባትየውም፡ “እንዴ ቆይ፡ ልጄ ሆይ! ገንዘቤን ትመልሳለህን? ” በጭራሽ አላለውም። ስለ ኃጢአቱ ምንም አላስከፈለውም። ተመልሶ በመምጣቱ ደስተኛ ሆነ። ልጁ ነውና፡ ወደ ልቡ በመመለሱ እጅግ ደስ አለው። የገዛ ልጁ ነበረ። ወደ ቤቱ በሚመለስባት ጎዳና ስለነበረ ደስ አለው። አሁን፡ ኃጢአቱን አልደገፈም፡ ነገር ግን ወደ ልቡ ተመልሶ መጥቶ እንዲህ ብሎ መናገሩ ደስ አሰኘው፡ “በአምላኬና፡ በአባቴ ፊት በድያለሁ። ተነሥቼ ወደ እርሱ እሄዳለሁ።”

123 በሩቅም፡ ባየው ጊዜ፡ ወደ እርሱ ሮጦ ሳመው። እርሱም አላቸው፡ “የሰባውን ወይፈን እረዱ፡” ያለ ገንዘብ። “እጅግ ውድ ልብስ አምጡ፡” ያለ ገንዘብ። “ቀለበቱን አምጡለት፡” ያለ ገንዘብ፡ “በጣቱ ላይ አጥልቁለት። ይህ ልጄ ጠፍቶ ነበርና፡ አሁን ተገኝቶአልና፡ እንብላ፡ እንጠጣና ደስ ይበለን። ሞቶ ነበርና፡ ዳግመኛም ሕያው ሆነ። በእሱ ደስ ይበለን።”

124 ወዳጆች ሆይ፡ ለመዝጊያ ያህል፡ ይህን ልበል። የሚያረካ ብቸኛው ነገር፡ ብቸኛው እውነተኛው ነገር፡ አለ የተባለው ብቸኛው መልካም ነገር፡ በገንዘብ ሊገዛ አይችልም። በኢየሱስ ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር ነጻ ሰጦታዎች ናቸው፥ የነፍስ መዳን፣ ደስታ። ኑና ብሉ፡ ደስም ይበላችሁ።

**ገንዘብን እንጀራ ላይደለ? የድካማችሁንም ዋጋ** ለማያጠግብ **ነገር ለምን ትመዝናላችሁ? ተግታችሁ አድምጡኝ፡ መልካም የሆነውን... ብሉ፡ ሰውነታችሁም** በ**ጮማ ደስ ይበለው።**

ጆሮ**አችሁን አዘንብሉ፡** ወደ **እኔም ቅረቡ፥ ስሙ፡ ሰውነታችሁም በሕይወት ትኖራለች፥ የታመነችይቱን የዳዊትን ምሕረት፡ የዘላለምን ቃል ኪዳን ከእናንተ ጋር አደርጋ**ለሁ።

125 ዘላቂ የሆነ ሁሉ፡ መልካም ነገር ሁሉ፡ ደስ የሚያሰኝ ነገር ሁሉ፡ ዘላለማዊ የሆኑ ነገሮች ሁሉ፡ ነፃ ናቸው፡ ዋጋ አትከፍሉባቸውም። በዚህ መጽሐፍ ጽሑፎች መጨረሻ ላይ፡ እንዲህ ይላል፡- “የወደደም፡ መጥቶ ከሕይወት ምንጭ ውኃ በነፃ፡ እንዲያው ይጠጣ።” ያለ ገንዘብም፡ ያለ ዋጋም። ገንዘባችሁን ለማያጠግብ ነገር ለምን ታጠፋላችሁ፡ ነጻ የሆነውን፡ እርካታ ያለው እውነተኛውን ነገር፡ በፊታችሁ ለምን ይረክስባችኋል?

እንጸልይ።

126 በጸጥታና በጸሎት ውስጥ ሳላችሁ፡ በዚህ ሕንጻ ውስጥ፡ ዛሬ ጠዋት፡ ከዚያ ምንጭ ያልጠጡ፡ ይኖራሉን፡ የዓለም ምኞቶች አሁንም በውስጥህ ከሆኑ፡ የምትጠጣበት ሰፍራ፡ ወይም የገንዘብህ አራጣ፡ ዛሬ ጠዋት መቀየር ትፈልጋለህን? መጥተህ ከእግዚአብሔር ዘንድ፡ (ያለ ገንዘብም፡ ያለ ዋጋም)፡ ማርና ወተት፡ የወይን ደስታ መግዛት ትፈልጋለህን? እጃችሁን እንስታችሁ፡ “ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ በጸሎትህ፡ አሰበኝ፡” ትላላችሁን? እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወዳጄ። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወዳጄ። እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እህቴ። “ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ በጸሎትህ፡ አሰበኝ፡” የሚል ሌላ ይኖር ይሆን?

127 አንዳንዶቻችሁ ወጣቶች፡ አዎን፡ ኑሮአችሁን አባክናችኋል። እናት ለእናንተ በጸሎት ያሳለፈችውን ሰ—ሰ—ሰአታት፡ አባትህም እንዲሁ፡ የተደረገልህን ትምህርት ሁሉ፡ የዲያብሎስን መንሾካሾክ ለመሰማት፡ ሌላውን ሁሉ አባክነኸዋል። አሁን የአለምን ሙዚቃ፡ የአለምን ነገር ፈልገሃል። በአሳማዎች መኖሪያ እንደነበረው እንደ አጥፊው ልጅ፡ ወደ ልብህ እየተመለስህ ነው። ወንድም፡ እህቶች ሆይ፡ እጆቻችሁን እያነሣችሁ፡ እንዲህ ማለት ትችላላችሁን፡ “አምላክ ሆይ፡ አሰበኝ። ዛሬ ጠዋት፡ ወደ ልቤ መልሰኝ፡ ወደ የአባቴ ቤት ልምጣ”? ምንም አያስከፍላችሁም። እሱ እየጠበቃችሁ ነው። በደላችሁ ምንም ቢሆንም፡ “ኃጢአታችሁ እንደ ደም ቢቀላ፡ እንደ በረዶ ነጭ ይሆናል፡ እንደ

አለላ ቢቀላም፡ እንደ ባዘቶ ነጭ ይሆናል።” በመለኮታዊው ህልውናው ፊት፡ እጃቸውን የሚያነሱ አሉን?

128 የታመሙና የተቸገሩ፡ እንዲህ የሚሉ፡ “ጉ—ጉድጓድ ውስጥ ገባሁ። ሰይጣን—ክፉ አደረገብኝ። እሱ አንካሳ አድርጎኝ አሳምሞኛል፡ ወይም የሆነ ነገር። ዛሬ ጠዋት፡ የእግዚአብሔር የእምነት ሰንሰለት ወደ ልቤ እንዲገባ እመኛለሁ፡ መልካም በሚሏት በር እንደነበረው ሰው፡ ከዚህ ጉድጓድ ሰቦ ያወጣኛው።” እጆቻችሁን አንሱ። ሁላችሁንም፡ እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

129 ጌታ ሆይ፡ ለኃጢአታቸው ይቅርታ፡ እጃቸውን የሚያነሱትን፡ በዚህ ሰዓት፡ ወደ አንተ አቀርባቸዋለሁ። አንተ አምላክ ነህ፡ ብቻህን አምላክ ነህ። አሁን በተቀመጡበት ቦታ፡ በዚያ ተናግረሃቸዋል። የተሳሳቱ መሆናቸውን ያሳመንካቸው በዚያ ነውና፡ ቃልም ሰፍራውን ባገኘ ጊዜ፡ መንፈስ ቅዱስም ሊናገራቸው ጀመረ፡ እንዲህ በማለት፡ “ተሳስተሃል። ተመለስ፡ ወደ እግዚአብሔር ወደ አባት ተመለስ።” እነሆም ከዚህ ከምድራዊ የአሳማ መኖሪያ፡ ወደ አባት ቤት መምጣት እንደሚፈልጉ ለማሳየት፡ እጃቸውን አነሱ፡ በዚያም የተትረፈረፈ አለና፡ ምንም ነገር ማምጣት የማይጠበቅባቸው ቦታ ነው። ገጣሚው “በእጄ ምንም ሳላመጣ፡ በቀላሉ ወደ መስቀልህ ገባሁ፡” በማለት በደንብ እንደገለጸው። በመልካምነት፡ በትህትና፡ አምነውም መጥተው፡ ህይወታቸውን፡ ያስረከቡ። አንተም የተሻለውን መጎናጸፊያን ትደርባለህ፥ ቀለበት አምጥተህ፡ ጣቶቻቸው ውስጥ ታጠልቃለህ፥ የታረደውን በግ መናም ትመግባቸዋለህ። ይሁን፡ ጌታ ሆይ።

130 የታመሙና የተጠቁም አሉ። ችግረኞች ናቸው። ሰይጣን ጉድጓድ ውስጥ ጥሏቸዋል፡ ምንም ጥርጥር የለውም፡ ለቀዶ ጥገና ገንዘብ አሳጥቶአቸዋል። ምንም ጥርጥር የለውም፡ ምናልባትም፡ ብዙዎቹ ቀዶ ጥገና ማድረግ አልቻሉም። ምናልባት ሐኪሙ ብዙ ገንዘብ ቢከፈለውም፡ ችግሩን ማስወገድ አልቻለም። አንተ ግን አምላክ ነህ። እናም በዚህች ሰዓት፡ በመንፈስ ቅዱስ ቅባት ስር አሁን ተቀምጬ፡ እያንዳንዳቸውን እንድትፈውስ እጸልያለሁ። ከጭንቅላታቸው፡ እስከ እግራቸው፡ ጨርሰው ይፈወሱ።

131 የመደናቸው ደስታ፡ ጠፍቶባቸው፡ ከእንግዲህ ደስታ ማግኘት ካልቻሉ። ዳዊት፡ በጥንት ጊዜ፡ “የመዳኔን ደስታ መልሰልኝ” አለ። በድካም ምድር አንተ አለት ነህና፡ ለጨለመባቸውና ለደከሙት፡ ደስታና ሐሴት ይሁንላቸው። በዐውሎ ንፋስ ጊዜ መጠለያ ነህና። ዲያቢሎስ በሽታን ሁሉ እና ሚሳይል ሲወረውርባቸው፡ አንተ በዐውሎ ነፋስ ጊዜ መጠለያ ነህ። እግዚአብሔር ሆይ፡ ዛሬም፡ እንደዛ ይሁን፡ በኢየሱስ ስም እንለምናለንና። ኣሜን።

በለሰላሳ እና በእርጋታ ኢየሱስ ድምጹ ያሰማል፡
እኔን እና እናንተን፡ ይጣራል፡
ኃጢአትን ብንሠራም፡ ምህረትንና ይቅርታን ያደርጋል፡
ለእኔ እና ለእናንተ ምሕረት ያደርጋል።

ወደ ቤት ኑ...

132 አሁንም፡ ወደ መሠዊያው ወጥታችሁ፡ መንበርከክ ብትወዱ፡ እንጸልይላችኋለን፡ እንቀባችኋለን፡ ማድረግ የምንችለው ሁሉ እናደርጋለን። በደህና ኑ።

... የደከማችሁ፡ ወደ ቤት ኑ፥
በትጋት፡ በእርጋታ፡ ኢየሱስ ይጣራል፡
ኃጢአተኛ ሆይ፡ ወደ ቤት ና፡ ይላል!

133 ትወዱታላችሁን? ቴዲ፡ እባክህ ኮርድ ስጠን፡ “እወደዋለሁ፡ ቀድሞ ስለወደደኝ እወደዋለሁ።” ያንን መጫወት ትችላለህ?

134 የአገልግሎቱን ሂደት ከመቀየሩ በፊት፡ እስኪ ለአፍታ ያህል፡ ለክብሩ እንዘምር። ይህ አምልኮ ነው። መልእክቱ ወጥቷል። ስለተቀበላችሁት በጣም ደስ ብሎኛል። መልካም እንዲያደርግላችሁ ለምኑት፡ እኔ ስናገረው መልካም ሆኖልኛልና። ጸሎቴ ይህ ነው ለእኔ የተሰጠኝ ያኑኑ ብርሃን፡ እንዲናገራችሁ፡ ወደ እኔ በመጣበት በተመሳሳይ ብርሃን ወደ እናንተ እንዲመጣ እጸልይላችኋለሁ። ጌታ በልባችሁ ውስጥ ይባርከው። እሺ።

እወደዋለሁ፡

አሁን እየዘመርን፡ አይኖቻችሁ ዝጉ። እጆቻችሁን ወደ ላይ አንሱ።

... እወደዋለሁ
ቀድሞ ስለወደደኝ
መዳኔንም ገዛሁ
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

135 አሁን ዝም ብለን አንገታችንን እናጎንብሰው፡ እናቀንቅን። ትወዱታላችሁን? እርሱ በልባችሁ እውነተኛ አይደለምን? በዚያስ ስለ እርሱ፡ አንዳች የሆነ መልካም ነገር የለምን? ቀድሞ ስለወደደኝ እወደዋለሁ፡ የህይወትን ምንጭ በቀራንዮ ዘንድ ጣለልኝ፡ በልቤ ውስጥ ተሰንቅሮ ቀረ።

136 እንዳትረሱ፡ ወንድም ድሩሞንድ ዛሬ ማታ፡ በጌታ እራት ምሽት ይሰብከናል። ጌታን ከወደዳችሁ፡ ኑና ከእኛ ጋር ውሰዱ። ጌታ ቢፈቅድ፡ እኔም ከእንናተ ጋር እገኛለሁ። እርሱም የወንድም ቶኒ ዛቤል-አማች-ነው፥ ወንድም ቶም ከአፍሪካ፥ ልጁ፡ ጥሩ ልጅ፥ እውነተኛ ጥሩ፡ ጠንካራ ክርስቲያን፡ ጥሩ ታዳጊ ሰባኪ ነው።

ቀድሞ ስለወደደኝ
መዳኔንም ገዛሁ
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

137 አሁን አንገታችንን ደፍተን ሳለ፡ ፒያኖው ይቀጥላል።

138 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ወደ ሌላ አገልግሎት ለመግባት እያስተካከልን ነው፡ ጌታ ሆይ። ለልባችን ስለ ተናገረን ስለ መንፈስ ቅዱስ እናመሰግንሃለን። ጌታ ሆይ፡ ይህን ስላደረግህልን፡ ደስ ብሎናል። ቃልህም በከንቱ ወደ አንተ አይመለስ፡ ነገር ግን ሊሠራው የታሰበውን ይፈጽም። እውነተኛ ነገሮች እና ዘላቂ ነገሮች ሁሉ ከእግዚአብሔር እንደመጡ ለማወቅ፡ በልባችን ውስጥ ይደር፡ ያለ ገንዘብ፡ ያለ ዋጋ። ለምንድነው ስለ ነገሮች የምንታገለው፡ የሚጠፉ ነገሮች፡ የህይወት-እና-የሞት ጉዳይ እናደርጋቸዋለንና? ጌታ ሆይ፡ ለማይጠፉ ነገሮች፡ ዋጋም ስለማያስከፍሉን፡ አብዝተን እንታገል። ዋጋው በነጻ ተከፍሏልና፡ እነሆም “የተጠማ፡ ይምጣ፡” በማለት ይጣራል።

139 የዚህን አገልግሎት ሁለተኛው ክፍል ጊዜ ይባረክ። ስጠን፡ ጌታ ሆይ። እና ዛሬ ማታ ከእኛ ጋር ሁን። የጥምቀት ስርዓትም ባርከው። ታላቅ መፍሰስ

ይሁን። በተወደደ ልጅህ፡ በጌታ በኢየሱስ ሰም የሚጠመቁ፡ እነዚህ ሰዎች፡ በመንፈስ ቅዱስ ይሞሉ። ዛሬ ጠዋት፡ ስለ ኃጢአታቸው፡ ንሰሐ ለመግባት፡ እጆቻቸውን ያነሱትን፡ እነዚህ ሰዎች፡ አሁን ይምጡ፡ የጥምቀት ልብስ ለብሰው፡ ወደ ጥምቀት ገብተው፡ ኃጢአታቸው እንደተሰረየላቸው ለዓለም ያሰመሰክሩ። እነሆም ተጠምቀዋልና፡ ከመጽሐውፋ አይሰረዙም። ይሁን፡ ጌታ ሆይ።

140 ወንድም ድሩሞንድ ከዙፋኑ ትኩስ የሆነውን መልእክት ሲያመጣልን፡ ዛሬ ማታ ከሱ ጋር ሁን። በመንፈስ ቅዱስ ቀባው። ቅዱሱን የጌታ እራት ስንቀበልም ከእኛ ጋር ሁን። ልባችን ንጹህ እና ንጹህ ይሁን፡, በእኛ ውስጥ ምንም ብክለት አይኑር። የኢየሱስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻን። ይሁን፡ ጌታ ሆይ። ከመካከላችን በሽታን አሰወግድ፡ ደስታን እና ሰላምንም ሰጠን። በኢየሱስ ክርሰቶሰ እንጠይቃለን። ኣሜን።

እወደዋ...

141 ትወዱታላችሁን? አሁን እጆቻችሁን ወደ እርሱ አንሡ።

እወደዋለሁ
ሰለ...

አሁን እጆቻችሁን ዘርግታችሁ አጠገባችሁ ያለውን ሰው ጨብጡት።

... ቀድሞ... (ሩሰል፡ እወደዋለሁ። ዛሬ ብሞትም እንኳ፡ እወደዋለሁ።)

ገዛ...

አዎን፡ ዙርያችሁን እየዘረጋችሁ እጆችን ተጨባበጡ።

... መዳኔ
በቀራንዮ...

እሺ፡ ወንድም ኔቪል፡ ከቃሉ ጋር። እሺ።

59-0802 ያለ ገንዘብም ያለ ዋጋም
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org